# እኮ ለምን?

በትውልድ አገሯ ከወገኗ ጋር ትዳር መሥርታ፣
ልጆች ወልዳ ዘር አብዝታ፣
ፍቅርዬ የልጆቼ እናት እያለ ያማለላት ባሏ፣
በእሳት አቃጥሎ፣ አሲድ ረጭቶ ገዳይዋ ይሁን በኋላ?

የስደት፣ የችግር ኑሮን አብራ በመጋራት፣
እናትዬ እየተባለ እንዳልተዜመላት፣
ውጭ አገር ወስዶ፣ ወዳጅዋ፣ ባሏ፣ ይግደላት?
አልፎልን፣ ባህር ማዶ ጥሩ ኑሮ እንኖራለን በማለት፣
ከባል፣ ከልጆቿ ጋር፣ በኬኒያ፣ በግብፅ፣ በሱዳን
በአረብ አገራት በስደተኝነት በመንከራተት፣
የድል፣ የብርሃን ቀን፣ ሲሳካልን እናያለን እያለች፣
ባልዋን፣ ልጆቿን፣ ራሷን አፅናንታ በኖረች፣
የራሷን ፍላጎት፣ አምሮቷን ሁሉ ወደኋላ ትታ፣
ባሏን ልጆቿን፣ በምትችለው መጠን አስደስታ፣
በኖረች ሁሉን አሟልታ!

*እኮ ለምን ኢትዮጵያዊት መገደሏ!*
*በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በኦስትሬሊያ፣ በኒው ዚላንድ … ኗሪ*
*ኢትዮጵያዊ ባሏ፣*

ትዳሩ ጣእም አጥቶ፣ አብሮ መኖር ካልተቻለ፣
ተለያይቶ፣ በየቅል፣ ኑሮን ማካሄድ እያለ፣
የሶስት፣ የስደስት ወራት፣ የአንድ ዓመት ሕፃን እናትን፣
መግደል ጨክኖ! እናትዬ፣ እህቴ፣ ፍቅሬ ያላትን …
አሲድ ረጭቶ፣ ፊቷ ላይ፣ ሌላም አካሏን አበላሽቶ፣
በዚህ አሰቃቂ ድርጊት፣ ምን ደስታ ይገኛል ከቶ።
ዱሮም ከሆነ ግንኙነቱ፣ ከስደት መንደር ማምለጫ፣
ያሰቡበት ሲደርሱ፣ ዘዴ እንዴት አጡ ከግንኙነቱ መውጫ?

በድርቁ ምክንያት፣ ኢትዮጵያውያን ረሃብተኞች፣
የሚል ቅጽል ስም አንጋቢዎች፣
አሁን ደግሞ ሌላ ስም፣ የኢትዮጵያ ወንዶች፣ ሚስት ገዳዮች።
እኛ በኦስትሬሊያ ኗሪዎች፣ በባሎቻቸው እጅ የሞቱ፣
ብዙ እህቶች አጥተናል በየክፍለ ግዛቱ።

*እኮ ለምን ኢትዮጵያዊት መገደሏ!*
*በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በኦስትሬሊያ፣ በኒው ዚላንድ … ኗሪ*
*ኢትዮጵያዊ ባሏ፣*

ቤተሰቧንና፣ ራሷን ረድታ፣
የሰላም ኑሮ ተቀዳጅታ፣
ሠርታ፣ ተምራ፣ ለወገኗ ተስፋ ሰጥታ፣

ተመስገን! እፎይ! ገና ከማለቷ፣
እናትዬ፣ ፍቅርዬ፣ ሲላት በኖረ ባለቤቷ፣
እጅግ ይዘገንናል! መገደሏ መሞቷ።

ምነው ዝም አላችሁ፣ ወገኖቼ፣ ብዙዎቻችሁ፣
ይሄ አሰቃቂ ድርጊት፣ ይቁም በሉ እንጂ ያስተጋባ ድምፃችሁ!
የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ማህበራት፣
የክርስትና እምነት ማህበራት፣
የእስልምና እምነት ማህበራት፣
የተቃውሞ ድምፅ አሰሙ እንጂ በአንድነት፣
አውግዙ እንጂ፣ የዚህን ድርጊት ፈጻሚዎች፣
በስቃይ በባሎቻቸው እጅ ደማቸው ለፈሰሰው እህቶች።

*እኮ ለምን ኢትዮጵያዊት መገደሏ!*
*በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በኦስትሬሊያ፣ በኒው ዚላንድ ... ኗሪ*
*ኢትዮጵያዊ ባሏ፣*

ሴቶች ወንዶች በአንድነት እንሰለፍ ሰሌዳ ይዘን በየአገሩ፣
ወጣት ሴትና ወንድ ልጆቻችን ሕፃናቱ ሳይቀሩ፣
ኧረ እንበል፣ ተስማምተን በአንድነት፣
ይህ አሰቃቂ! አሳፋሪ! ድርጊት መቆም አለበት።
እስቲ ለምሳሌ ያክል፣ ያላያችሁ የሚቀጥለውን ተመልከቱ፣
በየድረ ገጹ፣ በየጋዜጣው፣ ዘግናኝ ታሪካችንን ሲያትቱ።

1. http://ethiopiaforums.com/woman-found-dead-under-a-bridge

2. http://ethiopiaforums.com/a-man-killed-his-wife-in-UK-because-she-refused-to-have-sex

3. http://ethiopiaforums.com/a-woman-killed-by-her-boyfriend-in-las-vegas-identified

4. http://www.zehabesha.com/?p=840

*እኮ ለምን ኢትዮጵያዊት መገደሏ!*
*በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በኦስትሬሊያ፣ በኒው ዚላንድ ... ኗሪ*
*ኢትዮጵያዊ ባሏ፣*

ማርታ ተሾመ
ከምዕራብ አውስትራሊያ